## በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎትና ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 046/2011

### መግቢያ

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስርዓትን ውጤታማ ፤ ቀልጣፋና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማስተዳደር እና የተሟላ ምዝገባ ለማካሄድ እንዲቻል፤ እንዲሁም ለአሰራሩ የህግ መሰረት እንዲኖሩት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከዚህ በፊት በክልሉ ወሳኝ ኩነት ስራ አመራር ቦርድ ጸድቆ ስራ ላይ የነበረዉ የምዝገባ አገልግሎትና ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2009 አግባብነት የለሌዉና በዉስጥ የነበረው የክፍያ ተመን ከፍ በማለቱ ተገልጋዮች ወደ አገልገሎት እንዳይመጡ እንቅፋት እፈጠሬ ሲሆን ይህ መስተካከል ያለበት በመሆኑ፤

በመስተዳደር ምክር ቤት በዉይይት የምዝገባና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች ለመነሻ የሚሆን የክፍያ ተመን ወስኖ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የመስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 59/1/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ-1

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎትና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 046/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2004 እና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የብሔራዊ መታወቂያ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1049/2009 ማለት ነው፤